# ዶሮና ሃምሳ እግር

Winny Asara
Winny Asara
Dawit Girma
Amharic
Level 3

(imageless edition)

ዶሮና ሃምሳ እግር ጓደኞች ነበሩ። ሁሌም ግን ይፎካከራሉ። አንድ ቀን ኳስ ለመግጠምና ማን እንደሚበልጥ ለማየት ወሰኑ።

ወደ ኳስ ሜዳ ሄዱና መጫወት ጀመሩ። ዶሮዋ ፈጣን ነበረች። ሃምሳ እግርም ግን ከሷ ይበልጥ ነበር። ዶሮ አርቃ ትለጋለች፣ ሃምሳ እግርም ከሷ አርቆ ይለጋል። ዶሮ መደካከምና መናደድ ጀመረች።

በፍጹም ቅጣት ምት ይዋጣልን ብለው ወሰኑ። መጀመሪያ ሃምሳ እግር በረኛ ሆነ። ዶሮ መታች፣ አንድ ጎል አገባች። በመቀጠል የሃምሳ እግር ተራ ሆነ። መምታትና ጎል አስቆጥሮ ማካካስ አለበት።

ሃምሳ እግር መታ፣ አገባ። ሃምሳ እግር አታሎ አልፎ አገባ። ሃምሳ እግር በጭንቅላቱ መታ፣ አገባ። ሃምሳ እግር አምስት ጎል አገባ።

ዶሮ በመሳቷ በጣም ተናደደች። በጣም አሳዛኝ ተሸናፊ ሆነች። ሃምሳ እግር መሳቅ መፈንደቅ ጀመረ ምክንያቱም ጓደኛውም ብትሆን እንዲህ ያለ ፈንጠዝያ ታበዛ ነበር።

ዶሮ በጣም ተናዳ ስለነበር አፏን ከፈተችና ሃምሳ እግርን ዋጠችው።

ዶሮ ወደቤቷ እየሄደች ሳለ የሃምሳ እግር እናት አገኘቻት። እናትየዋ ሃምሳ እግርም ‹‹ልጄን አይተሻል?›› ብላ ጠየቀቻት። ዶሮ በበኩሏ ምንም አላለች። እናትዬዋ ሃምሳ እግር በጣም ተጨነቀች።

ከዚያም እናትዬዋ ሃምሳ እግር ትንሽ ድምጽ ነገር ሰማች። ‹‹እርጂኝ እናቴ!›› እያለ የሚጮህ ድምጽ። እናት ሃምሳ እግር አካባቢውን እየቃኘች በጥንቃቄ አዳመጠች። ድምጹ ከዶሮዋ ውስጥ እንደሚወጣ ተረዳች።

‹‹ልጄ ያለህን ልዩ ኃይል ተጠቀም!›› እናት ሃምሳ እግር ጮኸች። ሃምሳ እግር አስቀያሚ ሽታና አስከፊ ቃና መልቀቅ ጀመረ። ዶሮ ህመም ይሰማት ጀመር።

ዶሮ አገሳች። ከዚያ ዋጠችና ወዲያው አስታወከች። ከዚያም አነጠሰችና ሳለች። ደግማ ሳለች። ሃምሳ እግር አስጠሊታ ነበር!

ዶሮ በሆዷ ውስጥ ያለው ሃምሳ እግር እስኪወጣ ድረስ አሳላት። ተፈትልኮ ወጣ። ከዚያም እናትዬዋ ሃምሳ እግርና ልጇ ወደዛፉ ላይ ወጥተው ተደበቁ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዶሮዎችና ሃምሳ እግሮች ጠላቶች ሆኑ።

# Storybooks Canada

storybookscanada.ca

## ጶሮና ሃምሳ እግር

Written by: Winny Asara
Illustrated by: Winny Asara
Translated by: Dawit Girma

This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks Canada in an effort to provide children's stories in Canada's many languages.

This work is licensed under a Creative Commons
Attribution 3.0 International License.